2014 ዓ.ም

# የኃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ መመሪያቁጥር 121/2014

*አዲስ አበባ*
*የአዲስ አበባ ምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን*

# ማውጫ


መግቢያ........................................................................................................2
ክፍል አንድ..................................................................................................2
ጠቅላላ.......................................................................................................2
1. አጭር ርዕስ..............................................................................................2
2. ትርጓሜ....................................................................................................2
3. የተፈፃሚነት ወሰን.......................................................................................7
4. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ስልጣን፣ ኃላፊነት፣ ተግባርና ግዴታ ......7
5. የተገልጋዮች ግዴታና መረጃ የማግኘት መብት..................................................9
6. ስለውክልናና ህጋዊ መረጃ ስለመስጠት..........................................................11
ክፍል ሁለት..................................................................................................12
የምግብና ጤና ነክ ተቋም የጤና ብቃት ማረጋገጥን..............................................12
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ....................................................12
8. ስለ ቅድመ ፈቃድ ቁጥጥር ስራ.................................................................13
9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ሂደት እና የደረጃ አሰጣጥ ........................14
10. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት....................................................15
12. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማግኘት ........................................15
ክፍል አራት..................................................................................................16
የተቋማት ኃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ እና የምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር..............16
14. ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ተቋማትና ምርት....................................................16
15. የቁጥጥር ስራ አፈፃፀም ሂደት.....................................................................16
16. የማሻሻያ ጊዜ ስለመስጠትና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ስለማስገባት ..........................17
17. የመጠጥ ውሃ ብክለትን መከላከልና መቆጣጠር ...................................................17
18. ስለ ናሙና አወሳሰድ..................................................................................18
19. በትምባሆ ጭስ ብክለትና በልኮል መጠጥ የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን መከላከልና መቆጣጠር19
20. የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ስለማድረግ.............................................................20
21. የገላ መታጠቢያ ቤት አያያዝ......................................................................20
22. እርምጃ አወሳሰድ....................................................................................20
ክፍል ስድስት................................................................................................25
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች.......................................................................................25
23. ስለ ንግድ ማስታወቂያዎች፣ፕሮሞሽንና የምርት ገላጭ ጽሁፍ..................................25
24. ስለተጠያቂነት.........................................................................................25
25. የመተባበር ግዴታ......................................................................................25
26. ተፈፃሚነት ስለሌላቸውና ስለተሻሩ ህጎች .......................................................26
27. የመመሪያው ተፈፃሚነት ............................................................................26

**መግቢያ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚያከናወነውን የምግብና የጤና ነክ ምርትና ተቋማት ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ስራን ማጠናከር የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ህገ-ወጥ ምርት፣ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ ምርት እና ህግን ያልተከተለ አገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት ለማህበረሰብ ጤና ስጋት አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑ፤

በፌደራል ደረጃ የወጣውን የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 60/2006 በዝርዝር ለማስፈጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2012 አንቀጽ 44 እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 97 መሰረት ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 121/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በደንቡና አዋጁ ያሉ የቃላት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) "አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ የምግብ፣የመድኃኒት፣የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 30/2004 ማለት ነዉ፤
   2) "የፌደራል አዋጅ" የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ማለት ነው፤
   3) "የፌደራል ጤና አዋጅ" የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2009 ማለት ነው፤
   4) "ደንብ" ማለት ለአዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒት፣የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ የወጣዉ ደንብ ቁጥር 60/ 2006 ማለት ነዉ፤
   5) ‹‹ባለስልጣን›› ማለት የአዲስ አበባ የምግብ፤ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማለት ነዉ፤

6) “ምግብ” ማለት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅቶ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ገበያ ላይ የዋለ ወይም ለህብረተሰብ አገልግሎት የቀረበ እጽዋት ወይም የእጽዋት ውጤት እና የእንስሳት ተዋጽኦ፣የምግብ ጨው፣ውሃ፣አልኮል ወይም ሌላ መጠጥ እና ለምግብ ማምረት ወይም ለማከም የሚውል ማንኛውንም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ መድሀኒትን፣የውበት መጠበቂያና ትንባሆን አያካትትም፤

7) ‹‹የምግብ ደህንነት›› ማለት ምግብን በተገቢዉ መንገድ በማምረት ፤ በማዘጋጀት፤ በመያዝ፤ በማከማቸትና በማጓጓዝ እንዲሁም ለተጠቃሚዉ በማቅረብ ሂደት ምግብ-ወለድ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ነዉ፤

8) ‹‹ለብክለት ተጋላጭ ምግብ›› ማለት በሽታ አምጪ ለሆኑ ጥቃቅን ሕዋሳት ዕድገት ወይም ለመርዞች መመረት የተመቻቸ ወይም የተጋለጠ ምግብ ነዉ፤

9) ‹‹መከለስ›› ማለት ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ላይ ሌላ ነገር መጨመር ወይም ይዘቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይም በተገበቢዉ መንገድ በንጽህና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ ነዉ፤

10) ‹‹የምግብ ጭማሪዎች›› ማለት እንደ ምግብ አካል ተቆጥሮ ምግብን ለማጣፈጥ፤ ለማቅለም ፤ ሳይበላሽ ለማቆየት ወይም ለማሳመር የሚረዳ በምግብ ላይ የሚጨመር ማንኛዉም ንጥረ ነገር ነዉ፤

11)‹‹ ማሸጊያ›› ማለት ምግብን ወይ ጤና ነክ ምርትን በዉስጡ ለመሙላት ወይም ለመክተት ወይም ለመጠቅለል የሚያገለግል ማንኛዉም መያዣ ሲሆን ከምርቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸዉን መያዦዎችና ለመጠቅለያ የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎችን ይጨምራል፤

12)‹‹ገላጭ ጽሁፍ›› ማለት ህብረተሰቡ በቀላሉ በሚረዳዉ ቋንቋ የተጻፈ ሆኖ ስለ አንድ ምርት አስፈላጊዉን መረጃ የሚገልጽ በማሸጊያዉ ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ጽሁፍ ሲሆን በማሸጊያዉ ዉስጥ በአባሪነት የሚካተተዉን ጽሁፍ ይጨምራል፤

13)‹‹የአልኮል መጠጥ›› ማለት በማናቸዉም የአልኮል ይዘቱ ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ በላይ የሆነ የመጠጥ አይነት ነው ፤

14)«የምግብ ንግድ›› ማለት ምግብንና የምግብ ጥሬ እቃዎችን ለንግድ ማምረት፤ ማዘጋጀት፤ ማጭረር፤ ማሸግ፤ ማከመቸት፤ ማከፋፈል፤ ማጓጓዝ፤ በጅምላና በችርቻሮ መሸጥ ሲሆን የምግብ ጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪ ሥራዎችን ይጨምራል፤

15)‹‹የምግብ ተቋም›› ማለት በምግብ ማምረት እና አገልግሎት አሰጣጥ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛዉም ድርጅት ነዉ፤

16)‹‹ምግብ አዘጋጅ›› ማለት በማንኛዉም ምግብ አቅራቢ ተቋማት ዉስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከምግቡ ጋር ግንኙነት ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ ነዉ፤

17)‹‹ቆሻሻ›› ማለት ከኢንዱስትሪዎች፤ ከእርሻ ቦታዎች፤ ከትምህርት ቤቶች፤ ከመኖሪያ ቤቶች፤ ከንግድ ስፍራዎች፤ ከጤናና ጤና ነክ ተቋማት፤ ከመጸዳጃ ቤት ወይም ከሌሎች መሰል ተቋሞች የሚወጣና በሰዉ ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማለት ነዉ፤

18)‹‹የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት›› ማለት ሰዉ በሚኖርበት አካባቢ የሚገኝ በአካላዊ እድገት ፤ በጤና ወይም በማህበራዊ አኗኗር ዘይቤ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማናቸዉም ሁኔታ ማለት ነዉ ፤

19)‹‹አደገኛ ኬሚካል›› ማለት በጥንቃቄ ካልተያዘ ወይም አገልግሎት ላይ ካልዋለ በሰዉ ጤና ላይ ከፍተኛ የጤና ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ሆኖ የምግብ፤ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ‹‹አደገኛ›› ብሎ በዝረዝር የሚለየዉ ኬሚካል ነዉ ፤

20)‹‹መርዛማ ቆሻሻ›› ማለት ታክሞ እንድገና ጥቅም ላይ ሊዉል የማይችልና ለሰዉ ልጅ ጤና ጎጂ የሆነ ማንኛዉም ዓይነት ቆሻሻ ማለት ነዉ ፤

21)‹‹ተላለፊ በሽታ›› በተለያዩ መንገዶች በፍጥነትም ሆነ በቀስታ በመዛመት አደገኛ ወረርሽኝ የሚያስከትል እና በወረርሽኝ የማይታወቁትን ጨምሮ ከዚህ በፊት የነበረ ወይም በአዲስ መልክ ሊከሰት የሚችል በሽታ ማለት ነዉ ፤

22)‹‹ኳራንታይን ››ማለት ለድንገተኛ ተላላፊ በሽታ ተጋልጠዋል ወይም በበሽታዉ ተይዘዋል ተብለዉ የተጠረጠሩ ሰዎችን ይኸዉ ሁኔታቸዉ እስኪረጋገጥ ድረስ በተለየ ቦታ እንዲቆዩ የማድረገግ አሰራር ነዉ፤

23)‹‹ ለይቶ ማቆየት›› ማለት በተላላፊ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሽታዉን ወደ ሌላ ሰዉ እንዳያስተላልፉ ለተወሰነ ጊዜ ለብቻ ተለይተዉ እንዲቆዩ ማድረግ ነዉ ፤

24)‹‹ተቋም››ማለት ማንኛዉም ቁጥጥር የሚደረግበት ጤና- ነክ ወይም ምግብ ምርት አምራች ወይም ምርቱን አከፋፋይ፣ቸርቻሪ እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ማለት ነው ፤

25)‹‹ጤና ነክ ተቋም ማለት›› ማንኛዉም ህብረተሰብ የሚገለገልበት ተቋም ሲሆን የጤና ነክ ምርት አምራቾች፣ት/ቤት ፤ማረሚያ ቤት ፤የአረጋዉያን መንከባከቢያ

ማዕከል፣ የህጻናት ማሳደጊያ ማእከላት፣ የህጻናት ማቆያ ማዕከላት፣ መዋዕለ ህጻናት፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ቦታዎች፣ የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች፣ መታሻ ማእከላት፣ መዝናኛ ቦታዎች፣ የዉበት ሳሎኖች፣ የመዋኛ ስፍራዎች ፣የጸረ-ተህዋሲያን ርጭት አገልግሎት፣ የጤና ማማከር አገልግሎት፣ በጥቅሉ እዚህ ያልተጠቀሱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሰዉ ጤና ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማትንም ይጨምራል ፣

26)‹‹ሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ›› ማለት በሥራ አካባቢ የሚከሰቱ ወይም ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ ኬሚካላዊ፣ ፊዚካላዊና ሥነ ሕይወታዊ ጎጂ ንጥረ ነገሮች በመከላከልና በመቆጣጠር ሠራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ የሳይንስና ቴክኖሎጂ አስተዳደራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰራተኞችን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል አሰራር ማለት ነዉ ፣

27)‹‹የቅድመ ፈቃድ ቁጥጥር›› ማለት የምግብና ጤና ነክ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ወይም ለማደስ በቅድሚያ በተቆጣጣሪ ባለሙያው በመስክ ወይም ተቋሙ ባለበት ቦታ ተገኝቶ በመጎምኘት ከተቀመጠው መስፈርት ጋር በማነጻጸር ያሟላበትን ደረጃ የሚገለጽበት ተግባር ነው፣

28)‹‹የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት›› ማለት በወጣዉ የጤና ቁጥጥር ደረጃ ወይም መስፈርት መሰረት በምግብና ጤና ነክ ተቋማት ዘርፍ ስራ ለሚሰማራ ሰዉ ወይም ማህበራት የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፣

29)‹‹ናሙና›› ማለት የምግብንና ጤና ነክ ምርቶችን ለሰዉ ልጅ ተስማሚነት ጥራት ለማረጋገጥ ለሚከናወን ምርመራ የሚሰበሰብና ምርመራዉ የሚሰራለትን ምርት በሰዉ ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን የሚወክል ሲሆን መጠኑም የፌደራል ምግብና መድሀኒት አስተዳደር ባለስልጣን ባወጣው የናሙና አወሳሰድ መስፈርት ይሆናል፣

30)‹‹ማሸግ›› ማለት በአንድ ተቋም በጤና አጠባበቅ ጉድለት ወይም በሚሸጠው፣በሚያመርተው ምርት የደህንነትና ጥራት ችግር ምክንያት በሕዝብ ጤንነት ላይ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ሲገመት ሁኔታዎች እስከሚስተካከሉ ድረስ አገልግሎት እንዳይሰጥ አግዶ የማቆየት ተግባር ነዉ፣

31)‹‹ማስጠንቀቂያ›› ማለት በአንድ ተቋም ላይ በጤና አጠባበቅ ጉድለት ወይም በሚሸጠው፣በሚያመርተው ምርት የደህንነትና ጥራት ችግር ምክንያት በሕዝብ ጤንነት ላይ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ሲገመት በቃል ወይም በጽሁፍ የሚወስድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ ፣

32)‹‹ማገድ›› ማለት የጤና አጠባበቅ ቁጥጥር ስራ በሚከሄድባቸዉ ተቋም ላይ ለእገዳ የሚዳርጉ ተግባራትን ፈጽሞ ሲገኝ ተግባራት እንዳያከናዉን ለተወሰነ ጊዜ በመከልከል አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

33)‹‹መሰረዝ›› ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን መሰረዝና ለንግድ ፈቃድ ሰጪ አካል በማሳወቅ የንግድ ፈቃድ ጭምር እንዲሰረዝ በማድረግ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

34)‹‹ተቆጣጣሪ አካል›› ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የቁጥጥር ተግባራትን የሚያከናዉን ከባለሥልጣን መ/ቤቱ እስከ ወረዳ ጽ/ቤት ድረስ ያለ የባለስለጣኑ መዋቅር ነዉ ፤

35)‹‹የጤና ተቆጣጣሪ›› ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የቁጥጥርና ብቃት ማረጋገጥ ተግባራትን እንዲያከናዉን በባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣን የተሰጠዉ ባለሙያ ነዉ፤

36)‹‹መታወቂያ ካርድ ›› ማለት በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚዘጋጅና በቁጥጥር ሥራ ላይ ለሚሰማራዉ የጤና አጠባበቅ ተቆጣጣሪ /ኢንስፔክተር ስልጣንና ኃላፊት የሚያረጋግጥ ልዩ መለያ ካርድ ነዉ ፤

37)‹‹ጸረ-ተህዋሲያን ኬሚካል›› ማለት ሰውን ከሚጎዱ ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል እና ለመጠበቅ ሲባል በመኖሪያ፣በስራ አካባቢና ቁሳቁስ ላይ በመርጨት ወይም በመቀባት የሚገኙ ተላላፊ በሽታ አምጭ ተህዋሲያንን ለማዳከም ወይም ለማጥፋት የሚያገለግል ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገር ዉህድ ነዉ፤

38)‹‹አስመስሎ ማቅረብ›› ማለት የምግብ ማሸጊያ፤ መለያ ፤ የንግድ ምልክት፤ የንግድ ስም ወይም ማንኛዉንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም የአንድን ምርት ምንነትና ምንጭ ሆነብሎ አሳሳች በሆነ መንገድ ማሸግ ወይም ገላጭ ጽሁፍ በመለጠፍ እና ይህንኑ በሀሰተኛ መንገድ የታሸገ ወይም ገላጭ ጽሁፍ የተደረገለት ምርት በትክክለኛ አምራቹ እንደተመረተ በማስመሰል ማቅረብ፤

39)‹‹ ሰዉ›› ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፤ ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለጸዉ አነጋገሪ ሴትንም ይጨምራል፤

40)"ይዘት" ማለት ማንኛውም የምግብ እና ጤና ነክ ምርቶች በወጣላቸው የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት በውስጣቸው ሊይዛቸው የሚገቡ ንጥር ነገሮች ማለት ነው፤

41)"አምራች ተቋም" ማለት ማንኛውም በከፍተኛ፤ በመካከለኛና በአነስተኛ ደረጃ የምግብ ወይም ጤና ነክ ምርቶችን በማምርት ወይም በማቀነባበር የሚስራ ተቋም ማለት ነው፤

42)"እንደገና ማሸግ" ማለት የምርት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ምግብን ወይም ጤና ነክ ምርቶችን በሌላ ተቋም መልሶ የማሸግ ሥራ ነው፤

43)“የጤና ነክ ምርት” ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት ሆኖ በማሸት፣ በማፍሰስ፣ በማቅለጥ፣ በመንፋት፣ በመርጨት፣ ወይም በተመሳሳይ፣ በሰውነት ክፍል፣ በልብስ፣ በቁስ፣ በወለል፣ በግድግዳና በአካባቢ ላይ የሚደረግ ሲሆን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደምግባት ለመጨመር፣ ቅርጽና አሰራር ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር የሚውል (ኮስሞቲክስ አይነቶች፣የእቃ/ወለል/ልብስ/እጅ/ገላ መታጠቢያ/ማጽጃ ሳሙናዎች ፣ የፊትና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ወዘተ…) ሲሆን በሽታን ለማከም፣ለመመርመርና ለመፈወስ ጥቅም ላይ የሚውልን አይጨምርም፤

44)‹‹የድህረ ገበያ ቅኝት›› ማለት የምግቦችንና ጤና ነክ ምርቶችን ደህንነት፣ ጥራት ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ለማረጋገጥ የሚሰራ የቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ተግባር ነው፤

45)‹‹የምርት ምዝገባ ››ማለት ተፈጻነሚነት ባለው መስፈርት መሰረት ቁጥጥር ለሚካሄድበት ምርት የሚሰጥ እውቅና ነው፤

46)‹‹አስገዳጅ መስፈርት›› ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድሀኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን መመሪያን እና ሌሎች ህጎችን ለማስፈጸም በወጣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅና ምርት ጥራትና ደህንነት መስፈርት ውስጥ ምግብና ጤና ነክ ተቋም ግዴታ መሟላት ያለባቸውና የእነዚህ ጉድለት ቢከሰት በሰው ጤናና አካል ላይ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ መስፈርቶች(የሰራተኛ ጤና ምርመራ፣የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ መስጫ ቁስ፣በመመሪያው በእዝል7 ለተጠቀሱት አምራች ተቋማት የምርት ጤናማነት ላብራቶሪ ምርመራ ማድረግ፣የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቁስ እና ህጋዊ ፈሳሽ ቆሻሻ የሚወገድበት መንገድ፣የመጸዳጃ ቤትና ውሃ አቅርቦት፣ከስራው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እራሱን የቻለ ግድግዳ፣ጣሪያ እና በር ያለው የመስሪያ ቤት፣በምርት ማሸጊያ ላይ ተገቢ መረጃ ማስቀመጥ) ናቸው፤

47)‹‹ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት ወይም ተቋም›› ማለት በአዲስ አበባ ምግብና መድሀኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ቁጥጥር እንዲደረግባቸው ኃላፊነት የተሰጠው የምግብና ጤና ነክ ምርት ወይም ድርጅት ማለት ነው፤

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ የምግብና ጤና ነክ ምርቶችና ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

## 4. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ስልጣን፣ ኃላፊነት፣ ተግባርና ግዴታ

1) የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ኃላፊነት፣ ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ በፌደራል አዋጅ ቁጥጥር 1112/2011 አንቀጽ 63 እና በደንብ ቁጥር 60 /2006 የተገለጸው የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ኃላፊነት፣ሥልጣን፣ተግባርና ግዴታ በዚህ

መመሪያ ተግባራዊ ይሆናል፤

ለ/ ቁጥጥር በሚደረግበት የምግብና ጤና ነክ ምርት አምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ በስራ ሰአት የመግባት፣ ፍተሻ የማካሄድ፣ናሙና የመውሰድ፣የማሸግ፣የላብራቶሪ ናሙና ምርመራ ውጤት እስኪታወቅ ምርቱን ለብቻ በመቁጠር ተለይቶ እንዲቀመጥ የማዘዝ ፣ ምልክት የማድረግ በህግ አግባብ ምርቱን የማገድ፣የመያዝ ምርቱና ከምርቱ ጋር የሚያያዝ ሌላ ነገር ካለበት ቦታ ሳይወጣ ወይም በምንም አይነት ሁኔታ ሳይቀየር እንዲከማች የማዘዝ፤

ሐ/ ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብና ጤና ነክ ምርት የሚመረተው ወይም አገልግሎት የሚሰጠው እውቅና ባልተሰጠ ተቋም ውስጥ ከሆነ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የመግባትና ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ፤

መ/ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ምርቶች ስለመያዙ የታወቀና የጫነው ምርት ህግን ያልተከተለ ከሆነ ማንኛውንም ማጓጓዣ የማስቆም የመመርመር፣መክፈት ፣ናሙና የመውሰድና ምርቱን የማገድና የመያዝ፤

ሠ/ ፈቃድ ባለው ተቋም ውስጥ ከተቋሙ ስራ ሰአት ውጪ ወይም በማንኛውም ቦታ ቁጥጥር በሚደረግበር ምርት ምክንያት የህብረተሰብ ጤናን ጉዳት ላይ የሚጥል ሁኔታ ስለመኖሩ በቂ ምክንያት ሲኖር የፍርድ ቤት ትእዛዝ እስኪወጣ ስለ ምርቱ ማስረጃ ሊጠፋ፣ሊበላሽ እና ሊሸሽግ የሚችል ከሆነ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የመግባት የመፈተሽና አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ እና ይህንን ባደረገ 48 ሰአት ውስጥ በአቅራቢያ ላለ ፍርድ ቤት የማሳወቅ፤

ረ/ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ሊይዝ ይችላል ብሎ ያመነበትን ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም ውስጥ ያሉትን ማንኛውንም ሰነዶች፣ማስታወሻዎች፣ደረሰኞች፣መዝገቦች፣ኤሌክትሮኒክ መዝገቦችን እና ሌሎች መዛግብቶችን ጨምሮ የመመርመርና ኮፒ የማድረግ ናሙና ወይም የምርቱን ይዘት ልኬት የመውሰድ፣ፎቶ ግራፍ፣ ቪዲዮ፣ ምስል፣ ህግ በሚፈቅደው አግባብ የመውሰድ፤

ሰ/ ተከልሷል፣ በማስመሰል ተሰርቷል፤ ህገወጥ ነው ወይም ለህብረተሰቡ ጤና አደገኛ ነው ሊያስብል የሚችል አሳማኝ በቂ ምክንያት ሲኖር በማንኛውም ምርት የላብራቶሪ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ምርመራው እንዲካሄድበት የማዘዝና እንዲህ አይነቱን ምርት የላብራቶሪ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ የማዘዝ፤

ሸ/ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶች የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው፣የተበላሹ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ ሆነው ሲገኙ በአግባቡ መወገዳቸውን አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፤

ቀ/ ትንባሆ ማጨስ ወይም መጠቀም በተከለከለበት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ውስጥ በማንኛውም ሰአት የመግባት፣ የመመርመር እና እርምጃ የመውሰድ፤

በ/ አልኮል መጠቀም በተከለከለበት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ውስጥ በተቋሙ የስራ ሰአት ሰአት የመግባት፣ የመመርመር እና እርምጃ የመውሰድ፤

2) የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያ ግዴታ

ሀ/ በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 63 የተገለጸው የጤና ተቆጣጣሪ ባለሙያ ግዴታ በዚህ መመሪያ ተግባራዊ ይሆናል፤

ለ/ ስራ ከማከናወኑ በፊት ማንነቱንና የመጣበትን መስሪያ ቤት፣ለምን እንደመጣ፣ቁጥጥር ወደ ሚደረግበት ተቋም ወይም ማጓጓዣ ገብቶ የመመርመር ስልጣን እንዳለው በመግለጽ የተቆጣጣሪ ባለሙያነቱን መታወቂያ ማሳየት አለበት፤

ሐ/ በተቋሙ ለሚወሰነው ውሳኔ ተቆጣጣሪ ባለሙያው ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት ወይም ተቋም እንደአስፈላጊነቱ ሰነዶች፣ ማስታወሻዎች፣ ደረሰኞች፣ መዝገቦች፣ ኤሌክትሮኒክ መዝገቦችን እና ሌሎች መዛግብቶችን ጨምሮ የመመርመርና ኮፒ የማድረግ ናሙና ወይም የምርቱን ይዘት ልኬት የመውሰድ ፣ፎቶ ግራፍ፣ቪዲዮ፣ምስል በመያዝና በመውሰድ አግባብ ላለው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

መ/ ተቆጣጣሪ ባለሙያው የተሰጠውን ስልጣን የሚተገብረው የዚህን ህግ አላማ ለማሳካትና በሚያግዝ ሁኔታ ህግ በሰጠው ወሰን መሰረት ሌሎች የሀገሪቱ ህጎችና የስነ ምግባር ኮዶችን በማክበር እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መሆን አለበት፤

ሠ/ የዚህን መመሪያ መጣስን ሲያውቅ እንደአግባቡ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፤

ረ/ በትጋት፣በታማኝነት፣በጥንቃቄ እና በተቻለ ፍጥነት ስራውን መፈጸም እና የበላይ ኃላፊን ትእዛዝ በማክበር የመስራት ግዴታ አለበት፤

ሰ/ በስራ ምክንያት የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

ሸ/ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት በተቻለ ፍጥነት መወጣት እንዲቻል በሚያመጣው ተቀባይነት ያለው አዳዲስ አሰራር ስርአቶችን ተቀብሎ የመፈጸም ግዴታ አለበት፤

## 5. የተገልጋዮች ግዴታና መረጃ የማግኘት መብት

### 5.1 መረጃ የማግኘት መብት

1) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመጠየቅና

አስፈላጊዉን መስፈርት ሲያሟላም የማግኘት መብት አለዉ፤

2) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረበ ተቋም የባለስልጣኑን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በሶፍት ኮፒ ወይም በሃርድ ኮፒ የማግኘት መብት አለው ፤

5.2. ግዴታ

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2 ፣አንቀጽ 43 እና በደንብ ቁጥር 76 ንኡስ አንቀጽ.1 ማንኛዉም ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም የጤና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ እና ምርቱም ሳይመዘገብ ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብና ጤና ነክ ምርት ማምረት/ማከፋፈል/አገልግሎት መስጠት/መሸጥ አይችልም፤

2) ማንኛዉም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂ ሰዉ በጉብኝት ወቅት ተቋሙን ለተቆጣጣሪዎች ክፍት ማድረግ አለበት፤

3) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም በሚሰማራበት ወይም በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ የተቀመጠዉን መስፈርት የማሟላት ግዴታ አለበት ፤

4) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የጤና ተቆጣጣሪ በብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ወይም በቁጥጥር ወቅት ስምምነት የሚገባቸዉን የዉዴታ ግዴታ ዉሎች የማከበር ግዴታ አለበት፤

5) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ላይ የሕዝብ ጤናን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚጎዳ ከማንኛዉም ተግባር የመቆጠብ ግዴታ አለበት ፤

6) ተገልጋዩ ለሚሰማራበት ወይም ለተሰማራበት የንግድ ስራ በስሙ የተመዘገበ / በሌሎች ተቋማት / ግለሰብ/ ያልተያዘ ቋሚ የስራ ቦታና የመኖሪያ አድራሻ ሊኖረዉ ይገባል፤

7) ማንኛዉም ግለሰብ/ ተቋም የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎትን ለማግኘት ወይም በቁጥጥር ወቅት ሲጠየቅ የሚያቀርባቸዉ ሰነዶች ትክክለኛ ሕጋዊነት ያላቸዉ መሆን አለባቸዉ ፤

8) ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ተቋም የሚያቀርባቸዉ ሰነዶች ኦርጅናል ቅጅዎችን ከፎቶ ኮፒ ጋር አብሮ በማቅረብ ለማናበብ የተሟሉ ሰነዶች ማቅረብ አለበት ፡፡

9) ከባለስልጣን መ/ቤቱ የወሰደውን የጤና ብቃት የምስክር ወረቀት ወቅቱን ጠብቆ ማሳደስ አለበት፡

10)ተገልጋዩ የተሰማራበት የስራ ዘርፍ ሲዘጋ ወይም የንግድ ዘርፍ ወይም የቋሙ አድራሻ ሲቀይር የወሰደውን የጤና ብቃት የምስክር ወረቀት መመለስ አለበት፤

11)ማንኛውም ምግብና ጤና ነክ ተቋም በምርቱ የደህንነትና ጥራት ላይ ያልተጠበቀ ችግር ሲገጥም ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ምርት ለሰው ምግብነት ወይም ሰውነት የማይስማማ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቋሙ የሰው ጤናና ደህንነትን በማይጎዳ መልኩ የመሰብሰብና የማስወገድ ግዴታ አለበት፤

12)በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 6 እንደተጠቀሰው ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ አምራች ተቋም የሚያመርተውን ምርት በዝርዝር የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፤

## 6. ስለውክልናና ህጋዊ መረጃ ስለመስጠት

1) በደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 92 እና በፌደራሉ አዋጅ 1112/2011 አንቀጽ 69 መሰረት ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋማት በባለስልጣኑ በዚህ መመሪያና በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ለተቆጣጣሪው አካል የሚጠየቀውን ለስራ አስፈላጊ መረጃ ማቅረብ አለበት፤

2) ከሀገር ዉጪ የተሰጡ ልዩ ልዩ ሰነዶች ኦርጅናልና ትክክለኛ ለመሆናቸዉ በኢትዮጵያ የዉጪ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሰነዱ በተዘጋጀበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ፅ/ቤት የተመሰከረ / Authentication/ መሆን አለበት፤

3) በሀገር ዉስጥ የተሰጡ ማንኛዉም ሰነድና ማስረጃ በሰነዶች ማረጋገጫ መስሪያ ቤት የተረጋገጡ ሆነዉ በጊዜ የተገደቡ ዉሎችና ሰነዶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያላለፈባቸዉ መሆን አለበት፤

4) የማንኛዉም ተቋም/ ግለሰብ ለሚሰማራበት የንግድ ዘርፍ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በዉክልና ለማግኘት ዉክልና የሚሰጠዉ ግለሰብ ተቋም ሕጋዊ እዉቅና ያለዉና ምንም ዓይነት ሕጋዊ/ አስተዳደራዊ ወሰን ወይም እገዳ ያልተጣለበት መሆን አለበት፤

5) የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በሰነዶች ማረጋገጫ መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ዉክልና የተሰጠዉ ሰዉ ሙሉ ውክልና ወይም ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማዉጣትና የማሳደስ፤ የመሳሰሉትን ጉዳዮች በዝርዝር ተጠቅሶ የተሰጠ የዉክልና ሰነድ ያለዉ መሆን አለበት፤

6) ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስለሰጠው፣ ስላገደው ወይም ስለሰረዘው የጤና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለህብረተሰቡ ወይም ለሚመለከተው አካል እንደ አግባቡ ያሳውቃል፤

## ክፍል ሁለት

## የምግብና ጤና ነክ ተቋም የጤና ብቃት ማረጋገጥን

### 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 6 እና በደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 76 መሰረት ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ስራ ከመጀመሩ በፊት ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

2) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው፡-

ሀ/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ሞልቶ ሲያቀርብ (በአዝል 2 ማመልከት)

ለ/ የአገልግሎት ክፍያ መክፈሉ ሲረጋገጥ ፤

ሐ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ፤

መ/ አመልካቹ የተሟላ ማመልከቻ ካላቀረበ ማመልከቻውን በድጋሜ አስተካክሎ ሊያስገባ ይችላል፤

ሠ/ ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ አምራች/አከፋፋይ/ቸርቻሪ ተቋም የሚያመርተውን ምርት በዝርዝር ሲያስመዘግብ፤

ረ/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂዉ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ የማህበሩ ህጋዊ የመመስረቻ ቃለ-ጉባኤና የቅርጫፎች ዝርዝር ከነሙሉ አድራሻቸዉ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ሲያቀርብ፤

ሰ/ ለፋይል አስፈላጊውን መረጃ(የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወይም የቤት ኪራይ ውል፣የግብር ከፋይነት ቁጥር ወይም ንግድ ፈቃድ፣የማህበር/አክሲዮን ከሆነ የምስረታ ቃለጉባኤ እና ህገደንብ ኮፒ፣ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣የሰራተኞች ጤና ምርመራ ካርድ፣በውክልና ለሚፈጸም የአገልግሎት ጥያቄ ህጋዊ ውክልና መረጃ፣ለአምራች ተቋማት የምርት ላብራቶሪ ምርመራ ውጤት እና የአሰራር ቅደም ተከተል(SOP)፣የሙያ ተኮር ስራ ለሚሰሩ ተቋማት(የማሳጅ፣የጤና ፣የሼፍ፣ የጥራት ምርመራ፣ወዘተ…) የሰራተኛው የትምህርት ማስረጃና ሙያ ፈቃድ) ይዞ ሲቀርብ፤

ሸ/ የማንነት መለያ የመታወቂያ ካርድ ወይም መንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርትና የተቋማት ወይም የማህበራት የምዝገባ ወይም ሕጋዊ ዕዉቅና ያለዉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ሲያቀርብ፤

ቀ/ ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ምርቶች ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማራ

ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም የትንባሆ ምርቶችን በተጨማሪ ለመነገድ ሲፈልግ ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማግኘትና ግዴታ ውል መግባት አለበት፤

በ/ ተቋሙ ከላይ በንኡስ አንቀጽ 7.2 ስር ከሀ እስከ ቀ የተቀመጡትን ያሟላ ስለመሆኑ በማረጋገጥ በስራ ክፍሉ የቅርብ ኃላፊ በፊርማ ሲረጋገጥ፡፡

## 8. ስለ ቅድመ ፈቃድ ቁጥጥር ስራ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 2ሀ መሰረት የቀረበው ማመልከቻ ትክክል ሆኖ ከተገኘ የስራ ክፍሉ ኃላፊ ከሁለት ያላነሱ የተቆጣጣሪ ባለሙያዎች አባላት ያሉት ቡድን በመመደብ በመስፈርቱ መሰረት በመመዘን ውጤቱን እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤
2) አመልካቹ ካመለከቱበት ጊዜ ጀምሮ በተቆጣጣሪ ባለሙያው ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመስክ ጉብኝት እንዲደረግለት በስራ ክፍሉ ቀጠሮ ይሰጠዋል፤የጉብኝቱን ጊዜ እንዲያውቅ ይደረጋል፤
3) አመልካቹ በተሰጠው ቀጠሮ መሰረት ሳይገኝ ቀርቶ በራሱ ጊዜ ቀጠሮ ቢያሳልፍ የሌሎችን አመልካቾች ቀጠሮ በማይጋፋ መልኩ በድጋሚ ቀጠሮ ያስይዛል፤
4) ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከተገመገመ በኋላ መስፈርት የማያሟላ ከሆነ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎቹ ለአመልካቹና ለቅርብ ኃላፊው ጉድለቱን ወዲያውኑ በጽሁፍ ያሳውቃሉ፤
5) ተቋሙ ጉድለቱን አስተካክሎ በድጋሚ በጽሁፍ ካቀረበ ለሁለተኛ ጊዜ ሊታይለት ይችላል፡፡የእያንዳንዱን ጉብኝት ቁጥጥር ውጤት ሁሉም ተቆጣጣሪዎች ተፈራርመውበት ፋይል ይደረጋል፤
6) አመልካቹ ለሶስተኛ ጊዜ የመገምገሚያ መስፈርቶችን ሳያሟላ ከቀረ ከመጀመሪያው ማመልከቻ ቀን ጀምሮ ከሶስት ወር በኋላ በድጋሚ በማመልከት የሚጠበቅበትን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት ቀጠሮ ተሰጥቶት ሊታይለት ይችላል፤
7) አመልካቹ አመልክቶ የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ በኋላ በራሱ ክፍተት/በወቅቱ አለመገኘት ምክንያት በሂደት ላይ እያለ መጀመሪያ ከከፈለበት ቀን ጀምሮ ሶስት ወር ካለፈው የጠየቀውን አገልግሎት ለማግኘት በድጋሚ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፤
8) በቅድመ ፈቃድ ቁጥጥር ሪፖርት መሰረት አዲስ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በአስገዳጅነት የተቀመጡ መስፍርቶችን አሟልቶ ከቀሪ መስፈርቶች ጋር በአጠቃላይ ለተቋሙ የተቀመጠውን መስፈርት ≥75% እና እድሳት ለማድረግም በአስገዳጅነት የተቀመጡ መስፍርቶችን አሟልቶ ከቀሪ መስፈርቶች ጋር በአጠቃላይ ለተቋሙ የተቀመጠውን መስፈርት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተቀመጠው ደረጃ እና እድሳት ሂደት መሰረት ማሟላቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፤

9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ሂደት እና የደረጃ አሰጣጥ

1) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም የጤና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በተቀመጠው ጊዜ ገደብ በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

2) የተቋሙ የጤና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት የሚደረገው አግባብነት ባለው አካል ካልተሰረዘ፣ካልታገደ እና በራሱ ፈቃድ አገልግሎት ካላቆመ ነው፤

3) ማንኛውም ነባር ተቋም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚያወጣቸውን በአስገዳጅነት የተቀመጡ መስፍርቶችን ካሟላ በዚህ አንቀጽ ከታች በንኡስ አንቀጽ 4-6 በተቀመጠው ደረጃ መሰረት የጤና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ሊደረግለት ይችላል፤

4) ማንኛዉም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠየቀ ተቋም እንደ ተቋሙ ዓይነት በባለስልጣኑ የወጣዉን ዝርዝር መስፈርት 75 በመቶና ከዛ በላይ የሚያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀ ይሰጠዋል፤ ደረጃዉም ‹‹ ሀ›› ሆኖ አረንጓዴ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሆናል ፤

5) ማንኛዉም የብቃት ማረጋገጫ የጠየቀ ተቋም እንደ ተቋሙ ዓይነት በባለስልጣኑ የወጣዉን ዝርዝር መስፈርት ከ(65-74.99) በመቶ የሚያሟላ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡ ደረጃዉም ‹‹ደረጃ ለ›› ሆኖ ቢጫ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሆናል ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚመደቡ ተቋመት የላሟሏቸዉን ቀሪ መስፈርቶች ማሟላት አለማሟላታቸዉን ለማወቅ በየሶስት ወር ልዩነት አራት ጊዜ የሚታዩና በአመት ወስጥ ወደ ‹‹ደረጃ ሀ›› መግባት ይኖርባቸዋል፤ ማንኛዉም የብቃት ማረጋገጫ የጠየቀ ተቋም እንደ ተቋሙ ዓይነት በባለስልጣኑ የወጣዉን ዝርዝር መስፈርት ከ (>50-64.99) የሚያሟላ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡ ደረጃዉም ‹‹ሐ›› ሆኖ ቀይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሆናል ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚመደቡ ተቋማት ያላሟሏቸዉን ቀሪ መስፈርቶች ማሟላት አለማሟላታቸዉን ለማወቅ በሶስት ወር ልዩነት አራት ጊዜ በቁጥጥር የሚታዩና በአመት ዉስጥ ወደ ‹‹ደረጃ ለ›› መግባት ይኖርባቸዋል ፤

6) ማንኛዉም የብቃት ማረጋገጫ የጠየቀ ተቋም እንደ ተቋሙ ዓይነት በባለስልጣኑ የወጣዉን ዝርዝር መስፈርት ከሃምሳ በመቶ በታች(<50%) ከሆነ የሚያሟላው የጤና ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አይስጠውም፤

7) ነባር ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት የሚካሄደዉ በበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ባለው ጊዜ ሲሆን ከጥር 1 እስከ የካቲት 30 ድረስ የመደበኛ ክፍያውን ሀምሳ በመቶ(50%)ተጨምሮ በቅጣት የእድሳት ሂደቱ የሚከናወን ይሆናል፤

8) ነባር ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 የተጠቀሰውን በቅጣት እድሳት ጊዜ ተግባራዊ ሳያደርጉ የቀረ እንደሆነ እና ከንኡስ አንቀጽ 4-6 የተቀመጠውን የደረጃ ማሻሻል ሂደት(ከቀይ ወደ ብጫ እና ከብጫ ወደ አረንጓዴ) በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ተግባራዊ ካላደረጉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤

## 10.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይዘት

1) የተቋሙ ባለቤት ስም
2) ተቋሙን የሚመራው ባለሙያ/ስራ አስኪጅ ስም
3) የተቋሙ ስምና አድራሻ
4) የተቋሙ አይነት እና የሚሰጠው አገልግሎት
5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን
6) የሰጠው የስራ ኃላፊ ስምና ፊርማ
7) የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ማህተም
8) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ አዲስ ወይም እድሳት መሆኑን የሚገልጽ
9) ተቋሙ ከመስፈርቱ ሲነጻጸር ያገኘው ውጤት ወይም ደረጃ
10) ማሳሰቢያዎች

## 11.የአድራሻ፣ የባለቤትነት፣ የባለሙያ እና ደረጃ ለውጥ

ማንኛውም ተቋም ወይም ሰው አግባብነት ካለው ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ ሳያገኝ የአድራሻ፣ የባለቤትነት፣ የክፍሎች ሽግሽግ ማድረግ እና ደረጃ ለውጥ ማድረግ አይችልም፤

## 12.ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማግኘት

1) ማንኛውም ተቋም ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው፡
   ሀ/ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን ምስክር ወረቀት ሲመልስ
   ለ/ የጠፋ ወይም የተቃጠለ ከሆነ ከፍትህ አካል ማስረጃ ሲያቀርብ
   ሐ/ የተቀመጠውን  አገልግሎት ክፍያ መጠን ክፍያ ሲፈጽም
   መ/ ተቋሙ በመጀመሪያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሲወስድ በነበረበት ደረጃ ምትክ ሊሰጠው ይችላል

## ክፍል ሶስት

### 13.ስለድኅረ ገበያ ቅኝት

1) በደንብ 60/2006 መሰረት ምግብና ጤና ነክ ምርቶች ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ደህንነትና ጥራታቸውን ለማረጋገጥ በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች በድህረ ገበያ ቅኝት የቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል፣ ከተጠረጠሩ ምርቶች ላይ ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ እንዲመረመር ያደርጋል፣ የምርቱን ጥራት ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤

2) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ምርቱ በሰው ጤና ላይ ጉዳት ያመጣል ተብሎ ከተወሰነ ተቋሙ በራሱ መሰብሰብ ይኖርበታል፣መሰብሰብ ያልቻለበት ሁኔታ ከተፈጠረ በተለያየ መንገድ ለተጠቃሚ በቂ መረጃ እንዲደርስ ይደረጋል፣በሚመለከተው አካል እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የተቋማት ኃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ እና የምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር

### 14.ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ተቋማትና ምርት

በከተማዉ አስተዳደር ዉስጥ በሚገኙ የምግብና ጤና ነክ ተቋማትና ምርት ላይ በመስፈርቱ መሠረት በየደረጃዉ በተመደቡ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

### 15.የቁጥጥር ስራ አፈፃፀም ሂደት

1) በፌደራል ጤና አዋጅ 661/2009 እና በፌደራል አዋጅ 1112/2011 እንደተጠቀሰው ባለስልጣን መ/ቤቱ ለቁጥጥር ስራ በሚያሰማራቸዉ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም በሥራ ሰዓት በመግባት የቁጥጥር ሥራ ያከናዉናሉ፤

2) ሆኖም ግን በማንኛዉም ሁኔታ ህብረተሰቡን ሊጎዳ የሚችል ሁኔታ ሲያጋጥምና በቂ መረጃ ሲኖር ከስራ ሰዓት ዉጭም ጨምሮ የቁጥጥር ስራውን በየደረጃዉ ባሉ ተቆጣጣሪዎች ይሰራል፣ ይህንንም ተቆጣጣሪ ባለሙያው ለሚመለከተዉ አካልና ሀላፊ በማሳወቅ ይሆናል፤

3) ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሁለት ያላነሱ አባላት ያሉት የቁጥጥር ቡድኖች በመመደብ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በሚዘጋጁ መስፈርቶችና ደረጃዎች መሰረት በምግብና ጤና ነክ ምርቶችና ተቋማት ላይ የቁጥጥር ስራ ያሰራል፤

4) የቁጥጥር ቡድኑ ቁጥጥር ለማድረግ ወደ ተቋም ሲሄድ ለተቋሙ ቀድሞ ማሳወቅ አይጠበቅበትም፤

5) ለቁጥጥር የተሰማራ ቡድን ከመስፈርት በመነሳት በተዘጋጀ የቁጥጥር ማድረጊያ መጠይቅ

በመመርኮዝ ስራውን ያከናውናል ክፍተቶችንም ለጉድለት ማሳወቂያ ተግባር የተዘጋጀ የመስሪያ ቤቱ ክብ ማህተብ ያለው ቅጽ በመጠቀም ተፈራርሞ ዋናውን ለተቋሙ በመስጠት እና ግልባጭ በመያዝ ያሳውቃል፤

6) ለቁጥጥር ስራ የተሰማራ ቡድን ከቁጥጥር በኋላ የተያዙ መረጃዎችን በፋይል ዉስጥ በማስገባት አደራጅቶ ይይዛል፣ሪፖርት ያደርጋል፤

7) የቁጥጥር ቡድኑ ቁጥጥር ለተደረገበት ተቋም ሰርተፍኬት ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን በመሙላት፣በመፈረምና ተቋሙን በማስፈረም በተቋማቱ በሚታይ ቦታ ላይ እንዲለጠፍ ይደረጋል፤

## 16.የማሻሻያ ጊዜ ስለመስጠትና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ስለማስገባት

1) ማንኛዉም የኃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ቁጥጥር የተደረገበት ተቋም ዉስጥ ጉድለት ሲገኝበት የጉድለቱ ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችለዉ ከሆነ ብቻ የማሻሽያ ጊዜ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የዉዴታ ግዴታ ሊሰጠዉ ይችላል፤

2) የማሻሻያ ጊዜ በጤና ተቆጣጣሪዉ የተሰጠዉ ተቋም በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉሰጥ የሚጠበቅበትን የማሻሻያ ተግባር መስራት አለበት፤

3) በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ የጉድለት ማሻሻያ አድርጎ ካልተገኘ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፤

4) የማሻሻያ ጊዜ የተሰጠዉ ማንኛዉም ተቋም በተሰጠው የጊዜ ገደብ ስለማሻሻሉ በተቆጣጣሪው አካል /የክፍሉ ኃላፊ/ ሳያረጋግጥ አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

## 17.የመጠጥ ውሃ ብክለትን መከላከልና መቆጣጠር

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 16 እንደተገለጸው ማንኛውም የመጠጥ ውሃ አቅራቢ ወይም አምራች ለተጠቃሚ የሚያቀርበው ወይም ለምግብ ማዘጋጃ የሚጠቅም የመጠጥ ዉሃ በኢትዮጵያ ደረጃ የተቀመጠውን የደህንነት ደረጃ ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪ ባለሙያ ከመጠጥ ውሃ ምርቱ ላይ ናሙና በመውሰድ ምርመራ ያደርጋል ፣የናሙና ዉጤቱ በህብረተሰቡ ጤና ላይ አስጊ ሆኖ ከተገኘ በአቅራቢ ወይም አምራች ላይ አስፈላጊዉን እርምጃ ይወስዳል፡

3) ማንኛዉም ሰዉ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የማዕድን ዉኃም ሆነ የታሸገ ዉኃ ከማንኛምዉም አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅት ለህብረተሰቡ ማከፋፈል ወይም በሽያጭ ማቅረብ አይችልም፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ደረጃውን ያልጠበቀ እና በመስፈርቱ የተቀመጠውን ገላጭ ጽሁፍ የሌለው ዉኃ ያሰራጨ ወይም ያከፋፈለ ድርጅት ላይ ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል፤

5) የምርት አያያዝና ስርጭት የምርቱ ደህንነት ስርዓት በተከተለ መልኩ መሆን አለበት (ለፀሐይ የተጋለጠ መሆን የለበትም፤ምርቱ መቀመጥ ባለበት የቅዝቃዜ መጠን መቀመጥ አለበት)፤

6) ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበት አገልግሎት ስጪ ወይም አምራች ተቋማት የሚጠቀሙበት የከርሰ ምድር ወሃ/ground water/ ካላቸው እውቅና ባለው ላቦራሪ ለመጠጥ ወይም ለሌላ አገልግሎት መዋል የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

7) ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበት አገልግሎት ሰጪ ወይም አምራች ተቋማት የሚጠቀሙበት ውሃ ምንጩ በመንግስት አካል ለከተማው ህብረተሰብ ለመጠጥ ተብሎ ከሚሰራጨው ውሃ ውጪ ከሆነ በዓመት ሁለት ጊዜ የፊዚኮ-ኬሚካል እና ባክቴሮሎጂካል ምርመራ ማድረግ አለባቸው፤

## 18.ስለ ናሙና አወሳሰድ

1) ማንኛዉም የምግብና ጤና ነክ ተቋም በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደት እና ቁጥጥር ሂደት(እንደአስፈላጊነቱ) የምርት ናሙና ማስመርመር እንደ አንድ ተግባር ተወስዶ የምርቱ ናሙና ምርመራ መደረግ አለበት (የባክቴሪዮሎጂ፣ የፊዚኮኬሚካል የቶክሲኮሎጂ እንዲሁም የምርት ይዘቶች).የናሙና ማስመርመር ሙሉ ወጪን በተቋሙ ባለቤት የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ዝርዝር ናሙና ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ምርቶች ከታች በዕዝል 07 የተገለጹትንና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ምርቶችንም ይጨምራል፤

2) በማንኛዉም የኃይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ እና ምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ወቅት አጠራጣሪ የሆኑ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ወይም ጥቆማ ሲቀርብ ባለሙያዉ አጠራጣሪ ተቋም የምግብና ጤና ነክ ምርት ናሙና በተመሳሳይ ሁኔታ መዉሰድና ማስመርመር ይቻላል፤

3) ማንኛዉም ተቋም የሚያመርተዉን ምርት በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ወይም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ናሙና ወስዶ በቤተ ሙከራ ማስመርመርና ምርቱ የህብረተሰቡን ጤና የማያዉክ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ አምራቹ የራሱን ላቦራቶሪ ሊያደራጅ ይገባል ፡፡ አከፋፋይና እና ሻጫ ተቋማት ከአምራቹ የምርመራ ዉጤት ኮፒ መያዝ እና የገዙበት ህጋዊ ሰነድ መያዝ ይኖርባቸዋል፤

4) ለባለስልጣኑ ጥቆማ ሲቀርብና ለምርመራ የምግብና ጤና ነክ ምርት ከተወሰደ የምርመራ ዉጤት እስኪታወቅ ድረስ ምርቱ ለህብረተሰቡ እንዳይቀረብ ተቆጣጣሪ ባለሙያዉ በተቋሙ ዉስጥ በሚገኝ ክፍል ወይም ሌላ የማቆያ ክፍል ምርቱን በማስገባት ያሽጋል፤

5) በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 3 የተገለጸዉ ምርት ናሙና የቤተ ሙከራ /ላቦራቶሪ / የምርመራ ዉጤት ምርቱ በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰዉ የጤና ችግር እንዳለ የሚገልጽ ከሆነ ተገቢዉን አወጋገድ ስርዓት ተከትሎ እንዲወገድ ይደረገል፣ አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃዎችም ይወሰዳል፤

6) ተቆጣጣሪ ባለሙያዉ ናሙና በሚወስድበት ጊዜ ተገቢዉን የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎች/appropriate sampling technique/ መከተል አለበት፤

7) ማንኛዉም ተቋም ከሚያመርተዉ፣ከሚያከፋፍለዉና ከሚሸጠዉ ምርት ናሙና ተወስዶ በቤተ ሙከራ /ላቦራቶሪ/ ሲመርመር ለምርመራዉ የሚያስፈልገዉን ወጪ በሙሉ ተቋሙ ይሸፍናል፤

8) ማንኛዉም ተቋም አዲስ ምርት አምርቶ ወደ ገቢያ ከማቅረቡ በፊት ከምርቱ ናሙና ተወስዶ በቤተ ሙከራ /ለቦራቶሪ/ መመርመርና የህብረተሰቡን ጤና የማይጎዳ መሆኑ መረጋገጥ አለበት ፤

9) በማንኛዉም ተቋም ለህብረተሰቡ የሚቀርብ ዉሃ ደረጃዉን የጠበቀና ንጹህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቆጣጣሪ ባለሙያው በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ከዉሃ መጣሪያ፤ ማጠራቀሚያ ጋን ማሰራጫ ከቧንቧ ዉሃ መስመሮች እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች የዉሃ ናሙና በመዉሰድ በተቋሙ ወጪ ያስመረምራል፤

10) ማንኛዉም የመዋኛ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ጥቅም ላይ የሚዉለዉ ዉሃ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የዉሃ ናሙና በመዉሰድ በቤተ ሙከራ ያስመረምራል፤

## 19.በትምባሆ ጭስ ብክለትና በልኮል መጠጥ የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን መከላከልና መቆጣጠር

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 49 መሰረት የትንባሆ ምርት ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው መሸጥ፣ እንዲሸጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

2) ትንባሆ ማጨስ በተከለከለባቸው ቦታዎችና ቅጥር ግቢ (ት/ቤት፣የመንግስት ተቋማት፣ወጣት ማእከላት) 100ሜትር ዙሪያ ማንኛውም ተቋም የትንባሆ ምርት መሸጥ አይችልም፤

3) ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም የትንባሆ ምርትን በፍሬ መሸጥ አይችልም፤

4) በማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ውስጥ የሽሻ ምርትን ማምረት፣ ማከማቸት፣ ማስጠቀምና እና መጠቀም የተከለከለ ነው፤

5) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 49 መሰረት የልኮል መጠጥ ለተጠቃሚ ከመቅረቡ በፊት ተመርምሮ የተቀመጠውን ደረጃ ያሟላ መሆን አለበት፤

6) በፌደራል አዋጅ መሰረት የልኮል መጠጥ ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው መሸጥ የተከለከለ ነው፤

7) በፌደራል አዋጅ መሰረት የልኮል መጠጥ መሸጥና መጠቀም በተከለከለበት ቦታ መሸጥና መጠቀም እንዲሁም ማስጠቀም የተከለከለ ነው፤

## 20.የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ስለማድረግ

በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 68 መሰረት፡-

1) ማንኛውም ምግብና ጤና ነክ ተቋም ንፅህናው የተጠበቀ እና በቂ የመጸዳጃ ቤት ማዘጋጀትና በተቋሙ የስራ ሰአት ለደንበኞች ክፍት ማድረግ ይኖርበታል፤

2) ማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ንጽህናው የተጠበቀ በቂ የመጸዳጃ ቤት የማዘጋጀትና ለደንበኞች ክፍት የማድረግ ግዴታ አለበት፤

3) ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች አስተዳደሪ አካል በከተማ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ፍሳሽ ቆሻሻው በአግባቡ መወገድና ንጽህናቸው ሁል ጊዜ የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለበት፡

## 21.የገላ መታጠቢያ ቤት አያያዝ

በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 73 መሰረት፡-

1) ማንኛውም የህዝብ ሻወር ቤቶች አስተዳዳሪ አካል በከተማ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ ሻወር ቤቶች ፍሳሽ ቆሻሻው በአግባቡ መወገድና ንጽህናቸው ሁል ጊዜ የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

# እርምጃ

## 22.እርምጃ አወሳሰድ

22.1. አስተዳደራዊ እርምጃ፡

ባለስልጣን መስሪያቤቱ በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 65 እና በደንብ ቁጥር 60/2006 አንቀጽ 89 መሰረት በዚህ መመሪያ ከታች በንኡስ አንቀጽ ከሀ-ሰ የተጠቀሱትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፤

ሀ. የተበላሹ ምርቶችን ስለማስወገድ

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ 2

እንደተገለፀዉ ባለስልጣን መስሪያቤቱ በማንኛዉም ቁጥጥር በሚደረግባቸው የምግብና የጤና ነክ ተቋማት ዉስጥ የተበላሹና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸዉ ወይም ለጤና ስጋት በሆነ መንገድ የተመረቱ ምግብ እና የጤና ነክ ምርቶች በቁጥጥር ጊዜ ሲገኙ ወይም ተቋሙ እንዲወገድለት በጠየቀ ጊዜ የጤና ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ እንዲወገድ "ያደርጋል፣ ሙሉ ወጭውንም ባለንብረቱ የሚሸፍን ሲሆን ባለንብረቱ መሸፍንበት የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሌላ አግባብነት ባለው አካል ሊሸፈን ይችላል፤

2) በተቋሙ ወስጥ የተገኙ ምርቶች በተቋሙ የጤና ጉዳት በማያደርስ መልኩ መወገድ የሚችሉ ከሆነ ከባለቤቱ ጋር ወይም ከተወካይ ጋር ዕዝል ቁጥር 01 መሰረት በመተማመኛ ፎርም ተመዝግበዉ በመፈራረም እንዲወገዱ ይደረጋል፤

3) በተቋሙ ዉስጥ የተገኙ ምርቶች በድርጅቱ የጤና ጉዳት በማያደርስ መልኩ መወገድ የማይችሉ ከሆነ ወይም ለማስወገድ ምቹ ሁኔታዎች ከሌሉ ከተቋሙ ጋር ወይም ከተወካይ ጋር ዕዝል ቁጥር 01 መሰረት በመተማመኛ ፎርም ተመዝግበዉ በመፈራረም እስኪወገድ ድረስ በተለየ ክፍል ታሽጎ እንዲቀመጥ ይደረጋል፤

4) በተቋሙ ውስጥ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች ቢገኙበት ተቆጣጣሪ ባለሙያው እንደ ሁኔታዉ ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፤

5) የቁጥጥር ባለሙያዎች የተበላሹ ምግቦችን ወይም ሌሎች ጤና ነክ ምርቶች እንዲወገዱ ሲያደርጉ በአቅራቢያዉ ያለዉ የጸጥታ አካላት ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፤

6) ተቆጣጣሪው በዚህ መመሪያ መሰረት ለተወገደው ምርት በሚመለከተው አካል መረጃ ሲጠየቅ ይሰጣል፤

ለ. የቃል ማስጠንቀቂያ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

1) ማንኛዉም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ባለስልጣኑ ባወጣዉ መስፈርት መሰረት አስገዳጅ መስፈርቶችን አሟልቶ ሌሎች መስፈርቶች ላይ ጉድለት አሳይቶ ከተገኘ ፤

2) ማንኛዉም ተቋም በቁጥጥር ወቅት መያዝ ያለበትን መረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅና የተጠየቀው መረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት በወቅቱ የጤና ችግር ያልፈጠረ ከሆነና መረጃው በወቅቱ በተቋሙ ዉስጥ ካልተገኘ ፤(በአስገዳጅ መስፈርት ከተጠቀሱት ውጪ ያሉት ከሆኑ)፤

3) በቁጥጥር ወቅት በጉድለት ማሳወቂያ ቅፅ ወይም በዕዝል 04 የተቀመጠው ፎርም ተሞልቶ ከተሰጠ እንደ ቃል ማስጠንቀቂያ ተደረጎ ይቆጠራል፤

ሐ. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

1) ማንኛዉም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ባለስልጣኑ ባወጣዉ መስፈርት ውስጥ የአስገዳጅ መስፈርቶች ጉድለት አሳይቶ ከተገኘ፤

2) በቁጥጥር ወቅት በተቋሙ ምርት ማከማቻ ቦታ/ክፍል መጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት፣የተበላሸ ወይም ለጤና ስጋት የሆኑ ምርቶች ለብቻ ተመዝግበውና ተቆጥረው በሌላ ክፍል ወይም ቦታ ተለይተው የተቀመጡ ካልሆነ ፤

3) ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም በመጠጥ ውሃ ንጽህናና ጥራት ጉድለት፣በገላ መታጠቢያ፣የትምባሆ አየር ብክለትና በመጸዳጃ ቤት አያያዝ ብክለት ችግር ምክንያት በአካባቢና ሰው ጤና ላይ በተፈጠረ ብክለት አቤቱታ/ጥቆማ ቀርቦ በተቆጣጣሪ ባለሙያው ታይቶ ችግሩ ከተረጋገጠ፤

4) ማንኛዉም የምግብና ጤና ነክ ተቋም በወጣዉ መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ካላሳደሰና በመስፈርት ጉድለት ምክንያት በባለሙያዉ የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጉድለቱን በ 7 ቀናት ውስጥ ሳያሻሽል የቀረ እንደሆነ፤

5) ማንኛዉም ተቋም የምግብና ጤና ነክ ምርት ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ማስታወቂያ ሲሰራ በአንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 2 የተቀመጠውን አሰራር ጥሶ ከተገኘ፤

6) በማንኛዉም ተቋም የምግብና ጤና ነክ ምርት ላይ የሚያስቀምጠው ገላጭ ጽሁፍ በአንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በወጣ መስፈርት ላይ የተገለጹ ዝርዝሮችን ሳያሟላ ወይም መረጃ አዛብቶ ከተገኘ፤

7) መመሪያ አንቀጽ 22.3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ትምባሆ መሸጥ፣መጠቀምና ማጨስ በተከለከለባቸው ቦታዎች ማጨስ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ እና ተጓዳኝ ስእል ካለጠፈ ወይም ሲጨስ እርምጃ ያልወሰደ ከሆነ፤

8) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22.3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ትምባሆ መሸጥ፣መጠቀምና ማጨስ በተከለከለባቸው ቦታዎች ሲጨስ፣ጥቅም ላይ ሲውል እና ሲሸጥ ከተገኘ፤

9) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም በተላላፊ በሽታ በተያዘ ወይም ከምግብ ጋር ንክኪ ሊፈጥር የሚያሥችል ድንገተኛ አደጋ በደረሰበት ሰራተኛ ሲያሰራ ከተገኘ፤

10) በማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም አልኮል መሸጥ፣መጠቀምና ማስጠቀም በተከለከለባቸው ቦታዎች ጥቅም ላይ ሲውል እና ሲሸጥ ከተገኘ፤

11) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው አልኮልና ትምባሆ ሲሸጥና ሲያስጠቅም ከተገኘ፤

መ. ተቋሙን የሚያሳሽግ ሁኔታ

1) ማንኛዉም የምግብና ጤና ነክ ተቋም በወጣዉ መስፈርት መሰረት የታየበትን ጉድለት እንዲያሻሽል እና የብቃት ማረጋገጫ እንዲያድስ የሰባት ቀን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ሳያሻሽል ወይም ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ተቋሙ እንደሚታሸግ በተቆጣጣሪው የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለ24 ሰአት ከተሰጠው በኋላ ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ችግሩን እስኪያስተካክል ይታሽጋል፤

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22.1 ሀ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተቋሙ ዉስጥ የተበላሸ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ወይም አስመስሎ የተሰራ ወይም በዓድ ነገሮች ጋር የተቀላቀለ፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባልተሰጠው ሰዉ የተመረተ ምርት በቁጥጥር ወቅት ከተገኘ ተቋሙ ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ የማሸግ እርምጃ ይወሰድበታል፤

3) ማንኛውም የምግብና ጤና ነክ ተቋም የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ብቃት መረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው ሲሰራ ከተገኘ ፤

ሠ. ድንገተኛ እሽጋን በተመለከተ

1) ለተከሰተ ወረርሽኝ እና ብክለት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም መነሻ ምክንያት መሆኑ በሚመለከተው ባለሙያ ከታመነበት ወይም በተቋሙ ተገልጋዮች ድንገተኛ የበሽታ ስርጭት መጨመር መከሰቱ በባለሙያዎች ቡድን ከተረጋገጠ ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ችግሩን እስኪያስተካክል ይታሽጋል፤

2) ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም መጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበትና የተበላሸ ምርት መልሶ ሲያሽግና ገላጭ ጽሁፍ ሲያስተካክል ወይም ባእድ ነገሮችን ሲቀላቅል ወይም ቀላቅሎ ሲሸጥ ከተገኘ ወይም በተቋሙ ውስጥ ህገወጥ እርድ ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ከተገኘ ወይም ከተፈቀደለት ምርት ዉጭ ተያያዥ ያልሆነ ምርት ሲያመርት፣አገልግሎት ሲሰጥ ወይም ሲሸጥ ሲገኝ ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ችግሩን እስኪያስተካክል ይታሽጋል፤

3) ከማንኛውም ተቋም የተገለጋዩን ጤና የሚጎዳ መርዛማ ቆሻሻ/hazardous waste/ ከለቀቀ ማስተካከል እስከሚቻል ድርስ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከ30 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ችግሩን እስኪያስተካክል ይታሸጋል፤

ረ. እገዳን በተመለከተ

1) ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ተደጋጋሚ የጤና ጉድለትና ጥፋት የተገኘበትና ከአንድ ጊዜ በላይ የማስጠንቀቂያና እሽጋ ቅጣት የተወሰደበት ከሆነ የተሰጠውን የጤና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተነጥቆ ከ30 ቀናት እስከ 90 ቀናት የንግድ ፍቃዱ ታግዶ እንዲቆይ በደብዳቤ ለንግድ ፈቃድ ሰጪው አካል ይገለጻል፡፡ ቅጣቱንም ሲጨርስ ጉድለቶችን ማስተካከሉ ሲረጋገጥ ወደስራ እንዲገባ በጽሁፍ ይገለጽለታል፤

2) ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም/ምርት የተቀመጡትን መስፈርቶች ባለማሟላቱ በሰው ጤና ወይም አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ፤

ሰ. ስረዛን በተመለከተ

1) ተቋሙ በንዑስ አንቀጽ 22.1 /ለ--ረ/ የተጠቀሱ እርምጃዎች ተወስደውበት ሳያስተካክል ቀርቶ በባለሙያዉ የሙያ እይታ የጤና ጉድለት የተገኘበትን ተቋም የአካባቢ ጤና ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰረዛል፤

2) በአንቀጽ 22.1 ንኡስ አንቀጽ /ሀ--ረ/ የተጠቀሱት እርምጃዎች ተወስዶበት ያላስተካከለ ከሆነ ለሚመለከተዉ የንግድ ፍቃድ ሰጪ አካል እስከ መጨረሻዉ እንዲሰረዝ ያሳውቃል፤

3) ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም/ምርት የተቀመጡትን መስፈርቶች ባለማሟላቱ በሰው ጤና ወይም አካል ላይ በፈጠረው ጉዳት ሞት አስከትሎ ከተገኘ፤

22.2. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 66 በተጠቀሰው ሂደት መሰረት ማንኛውም ሰው በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣በአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ፣ በቁጥጥር ስራውና ከብክለት ጋር የተያያዙ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅር ከተሰኘ አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፤

22.3. የወንጀል ቅጣት እርምጃ፡

በዚህ መመሪያ የተመለከተን ገደብ፣መስፈርት፣ ሃላፊነትና ክልከላ ተግባር በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 67 እንዲሁም በወንጀል ህጉ ተሸፍኖ ያለ ተግባር እንደ ተግባሩ አግባብነት በእነዚህ ህጎች መሰረት በወንጀል ተጠያቂነት ይሆናል፤

22.4. ወደ ቀድሞ ህጋዊነት ስለመመለስ በተመለከተ

1) ማንኛዉም ተቋም በጤና ጉድለት ምክንያት ታግዶ ወይም ታሽጎ ቆይቶ የነበረበትን ጉድለት በማሻሻል እንደገና ወደ ነበረበት አገልግሎት ወይም ማምረት ስራ ለመመለስ ጥያቄ ሲያቀርብ በጽሁፍ የተገለፁት ችግሮች ማስተካከሉን ባሸገው አካል ጉድለቱ መስተካከሉ ከተረጋገጠ ወደ ህጋዊ ስራው ይመለሳል፤

2) ማንኛዉም ተቋም በጤና ጉድለት ምክንያት የብቃት ማረጋገጫው ከተሰረዘ፣ ከስድስት ወር በኋላ ሌሎች ተያያዝ ቅጣቶችን ጨርሶ በአዲስ መልክ ጥያቄ በማቅረብ መስፈርት አሟልቶ እንደገና ወደ ነበረበት አገልግሎት ወይም ማምረት ስራ ሊመለስ ይችላል፤

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23.ስለ ንግድ ማስታወቂያዎች፣ፕሮሞሽንና የምርት ገላጭ ጽሁፍ

1) በፌደራል አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በከተማ አስተዳደሩ ክልል ውስጥ የሚተላለፉ ከምግብ ጤና ነክ ምርትና አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ የንግድ ማስታወቂያዎችና ፕሮሞሽኖች በዚህ መመሪያ አንቀጽ ከታች የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤

2) የምግብና ጤና ነክ ምርትና አገልግሎት ማስታወቂያና ፕሮሞሽን ትክክለኛ፣ያልተዛባ፣ ተገቢ፣ስነ ምግባርን የጠበቀና ለምርቱ ወይም ለአገልግሎቱ የወጣውን መስፈርት ያገናዘበ መሆን አለበት፤

3) ገላጭ ጽሁፍን በተመለከተ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ተቋሙ ወይም ምርቱ አይነትና ይዘት በምርት ማሸጊያ ላይ መካተት ያለባቸው ገላጭ ጽሁፎች በማስፈጸሚያ መስፈርቶች ላይ በሚወጣውዝርዝር መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

### 24.ስለተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተጠቀሰውን ተላልፎ የተገኘ እና የተቀመጠውን ቅጣት ተግባራዊ ያለማድረግ በወንጀልና በፍትሐብሔር ያስጠይቃል፡፡

### 25.የመተባበር ግዴታ

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን ተግባር፣ኃላፊነትና ስልጣን በብቃት መወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፤

**26.ተፈፃሚነት ስለሌላቸውና ስለተሻሩ ህጎች**

1) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ አሰራሮችና መመሪያዎች በዚህ መመሪያ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም ፤

2) ቀደም ሲል ባለስልጣኑ ያወጣዉ የኃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5 /2010 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

3) የሆቴሎች፣ የሌሎች ምግብና መጠጥ ድርጅቶች እና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች መሰረታዊ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርቶች በሚል ጥቅም 2003 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የወጣዉ መመሪያም ተሽሯል፤

**27.የመመሪያው ተፈፃሚነት**

ይህ መመሪያ ከታህሳስ /2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር**

**ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**